# ትግላችን


አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት


በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## ችጋር በኢትዮጵያ


የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN



ቁጥር 1

መስከረም–ጥቅምት 1966



Vol ፫, ቁ፡ ፩, መስከረም-ጥቅምት 1966

ርዕሰ አንቀጽ

## አንድነታችን እንዲጠነከር፣ ትግላችን እንዳይጓደል

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ፣ በኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቅስቃሴ ውስጥ ፣ ከፍ ያሉ የፖለቲካ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ስለድርጅት፣ ፕሮግራም፣ ትግበር ፣ ርዕዮተ—ዓለም፣ • • • ወዘተ• በየቦታውና በየአቅጣጫው ብዙ ታትሟል፡፡ ወደፊትም እንደዚሁ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡

እንደዚህ መሆኑ ደስ ያሰኛል፡፡ ሁልጊዜና መቼም ወዴት ? እንዴት ? ለምን ? የሚሉት ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ የትም መቼም በተጠበቀ ሁኔታ እንድንነሳ ትምህርት ይሆኑናል፣ ይረዳናል፡፡

በዚሁ አኳያ የሚነሱት ጥያቄዎችና የሚደረጉት ውይይቶች፣ በአንድ በኩል ማህበርቸችንናጠቀሳሳው የተማሪ አንቅስቃሴ ያለበትንና የደረሰበትን የትግል ደረጃ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ከዚሁ ባሻገር ደግሞ ፣ የዕድገት ምልክቶችና አቅጣጫን አመልካቶች ናቸው፡፡ ልዩ ልዩ ሃሳቦችና አስተያየቶች በየቦታውና በየጊዜው ተራ በተራ እየተነሱና እየተፈጡ ሲሄዱ ፣ በተመጣጣኝ ደረጃ ደግሞ የፖለቲካ ጥራትን እንደሚያስከትሉ ዕውን ነው፡፡

እንደዚህ ሆኖ ሳለ፣ በዛሬው ወቅት በተማሪው አንቅስቃሴ ውስጥ —በተለይ ውጭ ሃገር በሚገኙት ተማሪዎች መካከል —ስለሃገር ቤት ጊዜያዊ ሁኔታ በቂ ዜና የለንምና—

በእንግሊዝ አገር የሚታተመው "OBSERVER" የተባለው ጋዜጣ መስከረም ዘጠኝ ዕለት በወጣው ጋዜጣ እንደገለፀው ከሆነ፣ የሞቱት ሰዎች ቁጥር ሃምሳ ሺህ —50·000— ደርሷል:: በትንሹ የተገመተ ነው:: ፍሬ መቁጠራችን ቁር ተ፣ሥራችን ሬሳ መቁጠር ከሆነ፣ ስምንት ዓመት ሙሉና ከዚያ በላይ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ያለቀውን ሕዝብ ማን ቆጥሮት ? ማን አስታውሶት? ብለን እንጠይቅ::

ከብቱም እንደዚሁ አልቋል:: የሚደርሱን ዜናዎች እንደሚያረጋግጡት አሁን ዝናብ ቢዘንብ እንኳ፣ የማረሻ ከብትም የለ፣ የዘር እህልም የለ፣ ሰውም ጉልበትም የለ::

ጉልበት "የተረፈው"ቢቀን፣ ትዓሩን፣ አያት ቅም-አያቶ የተቀበሩበትን መንደርና የትውልድ ሃገሩን እየተወ ተሰዷል፤ በመሰደዱ ላይ ነው:: በደረሱት ዜናዎች መሠረትና እንዳንዶችን ለመጥራት ያህል ከጋይንት፣ ከቀዱሳ ደላንታ፣ ከወረሂሙኑ፣ ከቦረና አውራጃዎች፣···በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ወለጋ ጠቅላይ ግዛትና በሾቁ ወደ ጅብትና ሜጫ አውራጃ ተሰደዋል:: በከተሞች ውስጥ አንኮበልቿ፣ደሴ፣ ሃይቅ፣ መርሳ፣ ወልዲያ፣···የረሃብተኞች ገተራ ሆነዋል::

የረሃቡ ዋና ምንጮች የበሰበሰው የፊውዳል ሥርዓትና ከቀኙናከግራ ደግፎ የያዘው የኢጆ አዞር አገዛዝ—በተለይ የአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ—ናቸዉ:: ረሃብ ሳጠቃቸው ሕጻናት፣ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ወጣቶች መቀጠያችን ለማቅረብ እንተባበር::"ረሃብ ቀጠሮ አያውቅም፣ ረሃብ ቀጠሮ አይሰጥም::"

"ትግላችን"

# ይዘት


1 ·ርዕሰ አንቀጽ 1

አንድነታችን ንጹሕነትነር
ትግላችን እንዲጠናከር ........

2 ·ሃገሬ መንግሥት ነባሬነት

በሕይወት ተፈር ጸሪያች .... 7

3 ·ፈሃበ፤ 'የዐጣቶች ማህበር'ና

ገሬቻው የሃይል ሥልጣን መንግሥት ........ 15

በዘይሬዲ ወገባ

4 · 'የኢትዮጵያ ወጣቶች አንድነትና ሥርዐት' .... 20

ተፈራ በሰው

........

5 ·ስሞች 'ክርስትና ቢነት' በታመነ ቢተው 32

6 ·ኢትዮጵያ በዓለም ጋዜጦች .......... 37

በማሞ ዘለቀ

8 ·የሽልማት አሸናፊዎች ስም ዝርዝር .......... 44

ስንሸው ቢዘ